# የገቢዎች ሚኒስቴር የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ




ጥቅምት 2015 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ

ክፍል አንድ ....3
1 መግቢያ ....3
ክፍል ሁለት ....5
2 የ2015 በጀት ዓመት የልማት ዕቅዱ እንድምታዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች....5
2.1 የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ታሳቢዎች ....5
2.1.1 የመንግስት የፊሲካል ፖሊሲ አቅጣጫዎች እንደ መነሻ....5
2.1.2 የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ እንደ መነሻ....6
2.2 ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች....6
2.3 ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራትና የሚጠበቁ ዉጤቶች ....8
ክፍል ሦስት....12
3 የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎች እና የድርጊት መርሃ ግብር....12
ክፍል አራት ....21
4 የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች....21
4.1 ዕቅዱን ለማሳካት በልዩ ትኩረት የሚሰሩ ስራዎች....21
4.2 የሪፖርት አቀራረብና የግንኙነት አግባብ....23
4.3 የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ....24
4.4 የግብረ- መልስ ሥርዓት....25

# ክፍል አንድ

## 1 መግቢያ

የገቢዎች ሚኒስቴር የፌደራል ሀገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ አፈጻጸምን ለማሻሻል እና ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን የሚያካሄድ፣ በጥናትና ምርምር ውጤት መሠረት ስትራቴጅዎችን የመቅረጽ፣ የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢ የመሰብሰብ አቅም ግንባታን በቀጣይነት የሚያረጋግጡና ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብን የሚያጠናክሩ የአሠራር ሥርዓቶችን የመቅረጽና የመተግበር፣ ታክስ ከፋዮች በፈቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባህላቸውን እንዲያዳብሩ የማገዝ፣ ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የመተንተን እና ጥቅም ላይ የማዋል፣ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሮች ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ የመስጠትና የታክስ አስተዳደር ስርዓቱ የሚጣጣምበትን ሁኔታ የመፍጠር እና በመጨረሻም ህገወጥ ንግድን በመቆጣጠር በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በአግባቡ ለመወጣት እየሰራ ይገኛል፡፡

ተቋሙ ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችል ለሀገራዊ ዕድገት እና ሁለንተናዊ ልማት አጋዥ የሆነ ለቀጣይ አስር ዓመታት የሚቆይ (2013-2022) የልማት መሪ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ስራ በገባው መሰረት ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ አመርታዊ ዉጤቶችን እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ የዚሁ ዕቅድ አንድ አካል የሆነው የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የሚቀዳና የተጣጣመ ሆኖ የሚዘጋጅ እንደመሆኑ መጠን በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ የማየት ርዕይ ላይ ለመድረስ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም ተቋሙ ወደዚሁ ርዕይ የሚያደርሰውን ተልዕኮ ማለትም ብቃት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ፍትሀዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት በመገንባት፣ ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ዕሴቶችን በመላበስ እየሰራ ይገኛል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት፣ የግብር ከፋዮችን የታክስ ሕግ ተገዥነት ማሻሻል እና ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ የሚሉ ስትራቴጂክ ግቦችንና ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራትን በማስቀመጥ እንዲሁም ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን በመቅረጽ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት ጉልህ ድርሻ የሚኖራቸው ታክስ በፈቃደኝነት መክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት፣ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣ የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር እና የዳበረ የስራ ባህል መፍጠር የሚሉትን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ተከትሎ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የተቋሙ ዋና ተልዕኮ የመንግስትን የልማት ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ገቢ መሰብሰብ እንደመሆኑ መጠን በ2015 በጀት ዓመት ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ከሀገር ውስጥ ታክስ ብር 266.95 ቢሊዮን እና

ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ብር 183.34 ቢሊዮን በድምሩ ብር 450.29 ቢሊዮን ለመሰብሰብ የሚያስችሉ እና በጥረት ተደራሽ የሚፈጸሙ ዝርዝር የገቢ ፊስካል ስራዎችን ለመፈጸም አቅዷል፡፡

ለዚህ ዕቅድ ስኬት የተቋሙ ሰራተኞች ሚና የማይተካና ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ምቹ የሆነ የስራ ከባቢ በመፍጠር፣ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማቸውን ከፍ በማድረግ፣ የተሻለ ውጤት ለሚያስመዘግቡ አመራሮችና ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነታቸውን ሊጨምሩ የሚችሉ ማበረታቻዎችን በየጊዜው በመስጠት ሁሉም አካላት ለውጤቱ እንዲረባረቡ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ዕቅዱ በክፍል አንድ መግቢያ፣ በክፍል ሁለት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበዉ ዉጤቶች፣ በክፍል ሶስት የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር እንዲሁም በአራተኛው ክፍል የአመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎችን የያዘ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2 የ2015 በጀት ዓመት የልማት ዕቅዱ እንድምታዎችና የሚጠበቁ ውጤቶች

### 2.1 የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ታሳቢዎች

በዚህ ክፍል ለተቋሙ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ እንደ መነሻ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሀገራዊ የመካከለኛ ዘመን (2015-2019) የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ እና ተቋሙ በ2014 በጀት ዓመት ያስመዘገባቸው ውጤቶች ለ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት ግብዓት በሚሆኑበት አግባብ እንደሚከተለው ተተንትነው በአጭሩ ቀርበዋል።

#### 2.1.1 የመንግስት የፊሲካል ፖሊሲ አቅጣጫዎች እንደ መነሻ

መንግስት በሀገሪቱ የተከሰተውን የተዛባ የማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛን ለማስተካከል ይረዳል ተብሎ የታመነበትን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ በማድረጉ ተስፋ ሰጪ የኢኮኖሚ ለውጦች መታየት መጀምራቸውን መረጃዎች አሳይተዋል። በሌላ በኩል የ2015-2019 የማክሮ ኢኮኖሚና ፊሲካል ማዕቀፍ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን የገቢ ሴክተሩ እነኝህን በመንግስት እየተወሰዱ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ለ2015 በጀት ዓመት የግብ ስኬት በትኩረት የሚንቀሳቀስ ይሆናል።

የፌደራል መንግስት ገቢ ከሶስት ዋና ዋና ምንጮች የሚገኝ ቢሆንም ዋናው እና አስተማማኝ የሆነው ገቢ ከታክስ ገቢ እና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚገኙ የገቢ ምንጮች ናቸው። በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ከነዚህ ምንጮች ሊገኝ የሚችለውን የፌዴራል መንግስት ገቢ ለማሳካት የሚያስችሉ ዝርዝር ታሳቢዎች የተለዩ ሲሆን አንዱና ዋናው ትኩረት የተደረገበት የታክስ ፖሊሲ ማሻሻያ በመሆኑ ለታክስ ገቢ አሰባሰቡ የሚኖራቸውን ተጨማሪ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በበጀት ዓመቱ በሥራ ላይ ለማዋል የታቀዱት ዋና ዋና የታክስ ህጎች የሚከተሉት ናቸው።

- **የተጨማሪ እሴት ታክስ ህግ፡-** በተጨማሪ እሴት ታክስ ውጤታማ የተመላሽ ስርዓትን በመዘርጋት በተመላሽ ምክንያት የሚባክነውን የመንግስት ገቢ ለማስቀረት የተጠናከረ የተመላሽ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲሁም ቀደም ሲል ያልተካተቱ አዳዲስ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በማካተት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ምንጭ የሚሰበሰበው ገቢ እንደሚጨምር ይጠበቃል።
- **የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያ፡-** ይህ ማሻሻያ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ ተጫማሪ አዳዲስ ዕቃዎች የሚካተቱ ሲሆን፣ በተጨማሪም በተመረጡ ኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ

የኤክሳይዝ ታክስ (Excise Tax Stamp) በመዘርጋት ከኤክሳይዝ ታክስ የሚገኘው ገቢ የሚጨምር ይሆናል፡፡

- **የንብረት ታክስ (Property Tax) ህግ፡-** አዲስ የንብረት ታክስ ህግ ተግባራዊ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን ከዚህ የሚገኘውም ገቢ 25 በመቶው ለፌዴራል መንግስት 75 በመቶው ደግሞ ለክልሎች እንዲሆን የሚያስችል ረቂቅ ህግ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ቀርቧል፡፡ ህጉ ጸድቆ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የታክስ መሰረቱን የሚያሰፋ እና የታክስ ገቢም እንደሚጨምር ይረዳል፡፡

- **የነዳጅ ኤክሳይዝ ታክስ፡-** በተለያዩ ምክንያቶች ስራ ላይ ሳይውል የቆየው የነዳጅ ኤክሳይዝ ታክስ ህግ ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ሲደረግ የገቢ አሰባሰቡን ያሳድጋል፡፡

በሌላ በኩል በታክስ አስተዳደሩ የሚወሰዱ የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ለገቢ አሰባሰቡ እድገት ቁልፍ ድርሻ ስለሚኖራቸው ተቋሙ በበጀት ዓመቱ ዕቅዱ ውስጥ አካቶ የሚተገብራቸው ይሆናል፡፡

### 2.1.2 የተቋሙ የ2014 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ እንደ መነሻ

ተቋሙ በ2014 በጀት ዓመት የታክስ አስተዳደር ተግባራትን በውጤታማነት ከመምራት አኳያ ማለትም ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ከማጎልበት፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ከመገንባት፣ የግብር ከፋዮችን የታክስ ሕግ ተገዥነት ሚናን በማረጋገጥ ዘላቂ የመንግስት ገቢን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዝርዝር የሪፎርም እና የገቢ ፊሲካል ስራዎች ግቦች ተጥለው አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም በዚሁ በጀት ዓመት የነበሩ ክፍተቶች ወደ ቀጣይ በጀት ዓመት እንዳይሸጋገሩ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ከወትሮው በተለየ መልኩ ተለጥጦ የታቀደና ተጨማሪ ጥረትን የሚጠይቅ በመሆኑ በየደረጃው ያለውን አመራርና ሰራተኛ በማንቀሳቀስ ርብርብ ማድረግን የሚጠይቅ መሆኑ እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡

## 2.2 ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች

በ2015 በጀት ዓመት የተነደፉት ተግባራት እንዲሳኩ ሁሉም የተቋሙ ማህበረሰብ ሊከተሏቸዉ የሚገባ መሰረታዊ አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

➡ **ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ**

በበጀት ዓመቱ ታክስና ቀረጥን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ለማሳደግ የግብር ከፋዩን ማህበረሰብ በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች በማስተማርና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በስፋት መስራት፣ በመደገፍ፣ ዕውቅና በመስጠት እና በተቋሙ ላይ ያለውን ግንዛቤ የሚጨምሩ ስራዎችን በተለያዩ መድረኮች በመስራት የሚጠበቅበትን የታክስና የቀረጥ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል

ሲሆን የታክስ ህግ ተገዥነት ባህሪ ለውጥ ማምጣት ባልቻሉ አካላት ላይ ተመጣጣኝ የህግ ማስከበር ተግባራት ተፈጻሚ የሚደረግበት ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል እንዲሻሻል ትኩረት ተደርጎ እንደ አንድ አቅጣጫ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### ➲ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ስርዓትን መገንባት

በ2015 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰቡን ሂደት ዲጅታል በማድረግ በኩል ግብር ከፋዩ ባለበት ቦታ ሆኖ የታክስ እና ቀረጥ ግዴታውን በኤሌክትሮኒክስ መንገድ አሳውቆ እንዲከፍል የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ የግብር ክፍያ ስርዓት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ እና በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ በሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ አቅም ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ረዥም ዕድሜ በማስቆጠር በስራ ላይ ያለውን የተቀናጀ የታክስ አስተዳደር ስርዓትን (SIGTAS) የሚተካ ዘመኑን የዋጀ ITAS ስርዓት በስራ ላይ የሚውልበትን ቅድመ ሁኔታ የማመቻቸት እና በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል፡፡

### ➲ የታክስ አስተዳደር ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ

የሀገራችን የታክስ አስተዳደር ስርዓት በኢ-መደበኛ ኢኮኖሚ፣ በህገ ወጥ ንግድ እና በታክስ ማጭበርበር ምክንያት ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሰብሰብ ያለበትን የታክስ ገቢ ለመሰብሰብ ካለማስቻሉም ባሻገር የንግዱ ማህበረሰብ በዕኩልነት ተወዳዳሪ እንዲሆን ያላስቻለ ሲሆን ይህም በሀገሪቱ ያለውን የሃብት ክፍፍል ኢ-ፍትሀዊ አድርጎት ቆይቷል፡፡ በመሆነም በሀገሪቱ የሚታየውን ያልተማከለ የንግድ ስርዓት ለማስተካከል ተቋሙ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ እየሰራ መቆየቱ እና በዚህም ረገድ ባለፉት የበጀት ዓመታት ከፍተኛ ስራዎች መሰራታቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በ2014 በጀት ዓመት የተሰሩ ጠንካራ የህግ ማስከበር ስራዎችን የበለጠ በማጠናከር እና ከአጋር እና ተባባሪ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራት በ2015 በጀት ዓመት የንግድ ኢፍታዊነትን በመከላከል የዜጎችን የጋራ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ኢኮነሚው የሚያመነጨውን ገቢ ለመሰብሰብ መስራት ያስፈልጋል፡፡

### ➲ የውስጥ እና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር

በ2015 በጀት ዓመት የታክስ አስተዳደሩን ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ከአጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ይጠበቃል፡፡ ይህም ሲባል ሀገር ውስጥ ካሉ ገቢ ሰብሳቢ እና የህግ አስከባሪ አካላት ጋር ህገ ወጥ ንግድና የታክስና ቀረጥ ገቢን ማጭበርበር ለመከላከል እና የታክስ ስርዓቱን ከማጣጣም አንጻር በቅንጅት መስራት /ለአንድ ዓላማ በጋራ መንቀሳቀስ/ የሚያስፈልግ ሲሆን የህገወጥ ንግድ ለመከላከል ከክልል መስተዳድር እና ከፌዴራል መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ከሀገር ውጪ ካሉ መሰል ገቢ ሰብሳቢ አካላት፣ ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የቴክኒክ ድጋፍና የልምድ ልውውጥ ማድረግ የሚያስፈልገው በመሆኑ ጠንካራ ቅንጅት መፍጠር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ይህ አቅጣጫ የቴክኒክ፣ የዕውቀት ሽግግር፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግን የሚጠይቅ በመሆኑ ተቋሙ በ2015 በጀት ዓመት አጋር አካላትን መለየት፣ ግንኙነት እና ስምምነት መፍጠር እና

በስምምነቱ መሰረት ለመፈጸም ሲያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን በጋራ ለይቶ በመፍታት ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

### ➲ የዳበረ የስራ ባህል ማምጣት

ተቋሙ የዳበረ የስራ ባህል ማምጣት የታክስ ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የተቋሙን ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዕሴቶችን የተላበሰ፣ ሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባ እና የዳበረ የስራ ባህል ያለው የሰው ኃይል ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ አቅጣጫ መነሻ በ2015 በጀት ዓመት የሰው ኃይል ስራ አመራር ልማት ስትራቴጂ ከመቅረጽ ጀምሮ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መሳብና ማቆየት፣ የምዘና፣ የማትጊያ እና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ ምቹ የስራ ከባቢ መፍጠር፣ ታማኝና ለስራ ተነሳሽ የሆነ አመራር እና ፈጻሚ ማፍራትን ይጠይቃል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን የማስፈጸሚያ ስልቶችን በስራ ላይ ለማዋል የዋናው መ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራሮችና ሰራተኞች ለአንድ ዓላማና ተልዕኮ የሚተጉ መሆናቸውን በመገንዘብ ስራዎችን በመደጋገፍ እና በመናበብ መርህ ለውጤት ማብቃት ይኖርብናል፡፡

## 2.3 ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራትና የሚጠበቁ ዉጤቶች

በ2015 በጀት ዓመት ለማሳካት የተለዩትን አራት ግቦች ለማሳካት የሚሰሩ ዋና ዋና ዝርዝር ስራዎች የተለዩ ሲሆን ተግባራቶቹ በአግባቡ ተፈጽመው የተቀመጡት ዓላማዎች ሲሳኩ የሚገኘው ውጤትም በእያንዳንዱ ግብ ስር እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

### ግብ 1. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት

**መግለጫ**

ይህ ስትራቴጂክ ግብ የተቋሙን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ማለትም የአሰራር ሰርዓቱን በማጠናከር፣ የአመራር እና የባለሙያን የአመራር ሰጪነትና የአፈጻጸም አቅምን በማሳደግ ለተገልጋዩ ማህበረሰብ ዕርካታ የሚጨምር አገልግሎት መስጠት አንዱ ሲሆን በሌላ በኩል የሰውና ቁሳዊ ሀብቱን ውጤት ማምጣት በሚችል መልኩ በማሰማራት የታለመውን ውጤት እንዲያመጡ ማስቻል ነው፡፡ ለዚህ ግብስኬት በዋናነት ተቋማዊ ወጥ የሆነና ተመጋጋቢ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ በተደራጀ መረጃ ላይ የተመሰረተ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፣ ወቅቱን የጠበቀ የአፈጻጸም ሪፖርት ለተቋሙ የዉስጥ አመራር እና ለተቆጣጣሪ አካላት የማስተላለፍ፣ የሰው ሃብቱን ስምሪት ውጤት ማምጣት በሚችል መለኩ ማደራጀት፣ ቁሳዊ ሃብቶችን ለታለመለት ዓላማ እንዲውሉ ማድረግና መከታተል፣ በአግባቡ ማስተዳደር፣ ውጤታማ የሆነ ስምሪት መስጠት፣ የተመደበን በጀት በፕሮግራሞች መደልደልና በአግባቡ ማስተዳደር፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን አጠቃቀምን ማሳደግ እና ዘመናዊ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘርጋትና ይህን አሰራር ተደራሽ የማድረግ፣ የአጋርነትና የህዝብ ግኑኙነት ስራዎችን ማጠናከር፣ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለተጠሪ ተቋማት ወቅታዊ

የሆነና ተከታታይነት ያለዉ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የሴቶች ተሳትፎን ማሳደግ፣ ማህበራዊ ኃላፊነትን መወጣትና ብልሹ ስነምግባርን እና ሙስናን መከላከል የሚያስችሉ ለግቡ ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽዎ ያላቸዉ እና በበለጠ ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የሚያስችሉ ዋና ዋና ስራዎች የሚሰሩበት ይሆናል። በግቦቹ ስር ያሉት ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል
- የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል
- የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል
- የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል
- የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል
- ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል
- የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል
- የሴቶችና ማህበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል
- የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል

እነኝህ ከላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ተግባራት በስራቸው በርካታ ዝርዝር ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች ያላቸዉ ሲሆን የነዚህ ዝርዝር ተግባራት ስኬት ወይም ውጤት ግቡን ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጽዎ አላቸዉ። በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት በእነኝህ ተግባራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

**ውጤት፡- ያደገ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የተሻሻለ ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ**

### ግብ 2. ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት

**መግለጫ**

የታክስ አስተዳደሩ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ቀላል፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ሲሆኑ ለግብር ከፋዩ እርካታን ከመጨመራቸዉም ባሻገር ታማኝ ግብር ከፋይ ለማፍራት የራሳቸው ጉልህ አስተዋጽዎ አላቸዉ። ስለሆነም የታክስ አስተዳደሩ የገቢ አሰባሰብ አሰራርን የላቀ ለማድረግ በዚህ ግብ ስር የህግ ማዕቀፎችንና አሰራሮችን የማሻሻል፣ የታክስ መረጃ አያያዝ ስርዓትን፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስርጭትን ተደራሽ ማድረግና አጠቃቀሙንም መቆጣጠር፣ የኤሌክትሮኒክ ታክስ ስርዓትን ማስፋትና ተደራሽ ማድረግ እና ለግብር ከፋዩ የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀላል፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊ፣ ወጪ ቆጣቢና ተደራሽ በማድረግ የተገልጋዩን እርካታ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት መፈጸም ይኖርባቸዋል።

- የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልህቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል
- የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን ማረጋገጥ
- የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል
- የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ

እነኝህ ከላይ የተቀመጡት ዋና ዋና ተግባራት በስራቸው በርካታ ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች የተቀረጹላቸዉ ሲሆን የነኝህ አመላካቾች ስኬት ወይም ውጤት የተቀመጠዉን ግብ ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጽዎ ይኖራቸዋል፡፡

**ውጤት፡- የተገነባ ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት**

## ግብ 3. የግብር ከፋዮችን የታክስ ህግ ተገዥነት ማሻሻል

**መግለጫ**

ሀገራዊ የታክስ ገቢን በላቀ ሁኔታ ለማሳደግ የህግ ተገዥነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ የህግ ተገዥነት ስራዎች ሲባል በዋናነት የስጋት ሥራ አመራር ስርዓትን አጠናክሮ በመተግበር እና ግብር ከፋዮችን ባላቸው የማሳወቅ ሁኔታ በመለየትና የስጋት ደረጃቸውን በመለየት፣ በተለዩ እና የስጋት ደረጃቸው ከፍተኛ ሆኖ በተገኙ ግብር ከፋዮች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግና የኦዲት ስራዎችን በመስራት የህግ ተገዥ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ በበጀት ዓመቱ ተጠናክሮ የሚሰራ ሲሆን ይህን የህግ ማስከበር ስራ በመስራት ህገወጥ ንግዶችን፣ ያለደረሰኝ የሚደረጉ ግብይቶችን እና ምንም ዓይነት ግብይቶች ሳይፈጸሙ የወጪ መጠን በመጨመር መክፈል ያለበትን የታክስ ገቢን ለመሰወር ወይም ለማጭበርበር የሚሰሩ ስራዎችን የመከላከል ሥራዎችን አጠናክሮ መስራት፣ የሀሰተኛ ደረሰኝ ስርጭቶችን መቆጣጠር፣ የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ ታክስ እና ቀረጥ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማሳደግ በሀገር ውስጥ ታክስ በኩል የሚሰራ ሲሆን በዚህ ግብ ስር የሚተገበሩት ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር
- የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ሥራዎችን ማጠናከር

**ውጤት፡ ያደገ የህግ ተገዥነት**

## ግብ 4. ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ

**መግለጫ**

መንግስት የቀረጸው የልማት ዕቅድ ፋይናንስ የሚያደርገው በዋናነት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው የሚሰበሰብ የታክስ ገቢ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ገቢ በብቃት መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት የሚፈጸሙ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ ታክስ እና ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ በአጠቃላይ ብር 450,292,248,448.14 ጥቅል ገቢ ለመሰብሰብ

ዕቅድ ተይዟል። በዕቅድ ከተያዘው ገቢ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ታክስ ብር 266,952,791,431.67 እና ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ብር 183,339,457,016.47 የሚሰበሰብ ይሆናል።

- ከሀገር ውስጥ ታክስ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ
- የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አቅም ማጎልበት

**ውጤት፦ ያደገ ገቢ**

# ክፍል ሦስት

## 3 የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎች እና የድርጊት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት | 15 | የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል (ክብደት=1) | ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | 0.4 | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | | | የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| | | | | የዘርፉን መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማደራጀት | 0.3 | በመቶኛ | 0 | 25 | | 5 | 15 | 25 |
| | | | የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል (ክብደት=2) | ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ | 0.5 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | | | ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ | 0.5 | በቁጥር | 2527 | 4800 | 798 | 1632 | 2050 | 320 |
| | | | | የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | 0.5 | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| | | | | የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 4.9 | 4 | | | | 4 |
| | | | የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር | የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል (ድርሻ) | 0.5 | በመቶኛ | 85.62 | 100 | 18.94 | 48.27 | 76.44 | 100 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=3) | ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 87.5 | 92 | 88 | 89 | 91 | 92 |
| | | | | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 30 | 60 | 10 | 25 | 50 | 60 |
| | | | | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 0 | 30 | | 5 | 15 | 30 |
| | | | | መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል | 0.5 | በመቶኛ | 0 | 80 | | | | 80 |
| | | | | የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ | 0.5 | በሚሊዮን ብር | 2.02 | 2.6 | 0.65 | 0.65 | 0.65 | 0.65 |
| | | | የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=2) | መረጃ ቋት ማደራጀት | 0.4 | በመቶኛ | 25 | 50 | | 30 | 40 | 50 |
| | | | | በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር | 0.3 | በመቶኛ | 0 | 100 | | 50 | 80 | 100 |
| | | | | በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አቶሜት ማድረግ | 0.3 | በመቶኛ | 13 | 33 | | | 25 | 33 |
| | | | | የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 79.3 | 85 | | | | 85 |
| | | | የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት=1) | መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | 1 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል (ክብደት=2) | የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.25 | በቁጥር | 1 | 2 | 1 | 1 | | |
| | | | | የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም | 0.25 | በቁጥር | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | | | የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.5 | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | | | |
| | | | | በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | 0.5 | በቁጥር | 1 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | | | ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት | 0.5 | በቁጥር | 926 | 1200 | 288 | 416 | 320 | 176 |
| | | | የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት=1) | በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ ማስተካከያ የተደረገባቸው | 0.25 | በመቶኛ | 95 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | | | ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ | 0.25 | በቁጥር | 20 | 120 | 5 | 40 | 40 | 35 |
| | | | | የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 95 | 100 | 96 | 97 | 98 | 100 |
| | | | የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነት ንና ተጠቃሚነ | የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 121 | 200 | 126 | 36 | 8 | 30 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | ትን ማሻሻል (ክብደት=1) | ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 39 | 42 | 40 | 40 | 41 | 42 |
| | | | | ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 915 | 1,969 | 367 | 682 | 690 | 230 |
| | | | | ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ መፍጠር | 0.25 | በመቶኛ | 64 | 85 | 67 | 70 | 80 | 85 |
| | | | የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት=2) | የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል | 0.5 | በቁጥር | 50,000 | 100,000 | | | | 100,000 |
| | | | | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በቁጥር | 0 | 30 | | | | 30 |
| | | | | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በሚሊዮን ብር | 0 | 7 | | | | 7 |
| | | | | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በቁጥር | 0 | 1,000 | | | | 1,000 |
| | | | | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በሚሊዮን ብር | 0 | 3 | | | | 3 |
| | | | | ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ | 0.3 | በሚሊዮን ብር | 60 | 21 | | 5 | 6 | 10 |
| | | | | የተደረገ ደም ልገሳ (ድርሻ ከሰራተኛ | 0.3 | በመቶኛ | 13.18 | 20 | | 10 | 15 | 20 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | | ብዛት) | | | | | | | | |
| | | | | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.15 | በቁጥር | 76 | 76 | 76 | 76 | 76 | 76 |
| 2 | ቀልጣፋ፣ ዘመናዊና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ማጎልበት | 25 | የገቢ አሰባሰብ አሰራር ልህቀትን ለማምጣት የህግ ማዕቀፎችን እና አሰራሮችን ማሻሻል (ክብደት=6) | ለፍትህ አካላት የሚቀርቡ የፍትሃብሔር ጉዳዮች በመዝገብ የመርታት አቅምን ማሳደግ | 3 | በመቶኛ | 89 | 97 | 94 | 95 | 96 | 97 |
| | | | | ለአቤቱታ የሚቀርቡ የፍትሃብሔር ጉዳዮች የመዝገብ ምጣኔ መቀነስ | 1.5 | በመቶኛ | 6.25 | 5 | 5.94 | 5.62 | 5.31 | 5 |
| | | | | በስጋት ከተለዩ ግብር ከፋዮች የግኝት ምጣኔን ማሳደግ | 1.5 | በመቶኛ | 73.88 | 87.5 | 17.73 | 41.31 | 66.05 | 87.5 |
| | | | የታክስ መረጃ አስተዳደር ውጤታማነቱን ማረጋገጥ (ክብደት = 5) | የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በመጠቀም Z-Report የሚልኩ ድርጅቶች ምጣኔን ማሳደግ | 1.5 | በመቶኛ | 92 | 95 | 95 | 95 | 95 | 95 |
| | | | | የግዥና ሽያጭ የታክስ መረጃ ጥራትና ብዛት ማሳደግ | 2 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | | | የገበያ ዋጋ መረጃ ማሰባሰብና አጠቃቀምን ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 99 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | | | የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተደራሽነትን ማስፋት | 0.5 | በመቶኛ | 77.6 | 79 | 79 | 79 | 79 | 79 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | የኤሌክትሮኒክ ታክስ (E-Tax) አጠቃቀምን ማሻሻል (ክብደት = 4) | በኤሌክትሮኒክ ታክስ የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮች ድርሻን ማሳደግ | 2 | በመቶኛ | 58 | 82 | 70 | 75 | 80 | 82 |
| | | | | በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የታቀፉ ግብር ከፋዮች ድርሻን ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 28 | 60 | 36 | 45 | 54 | 60 |
| | | | | በኤሌክትሮኒክ የታክስ ክፍያ ሥርዓት የተሰበሰበ የታክስ መጠን ከአጠቃላይ ታክስ ያለውን ድርሻ ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 13.09 | 25 | 25 | 25 | 25 | 25 |
| | | | የግብር ከፋዮች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ (ክብደት = 10) | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የምዝገባ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | | | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የተመላሽ አገልግሎት ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 91 | 95 | 95 | 95 | 95 | 95 |
| | | | | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የአገልግለኮት ኦዲት አገልግሎት ማሳደግ | 3 | በመቶኛ | 86 | 90 | 90 | 90 | 90 | 90 |
| | | | | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የክሊራንስ | 2 | በመቶኛ | 84 | 85 | 85 | 85 | 85 | 85 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | | አገልግሎት ማሳደግ | | | | | | | | |
| | | | | በስታንዳርዱ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት የተሰጠ የታክስ ቅሬታ ውሳኔ አገልግሎት ማሳደግ | 3 | በመቶኛ | 94 | 95 | 95 | 95 | 95 | 95 |
| 3 | የግብር ከፋዮችን የታክስ ሕግ ተገዥነት ማሻሻል | 20 | የታክስ ማስታወቅና ክፍያ አቀራረብን ማጠናከር (ክብደት = 5) | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በአማካይ ግብራቸውን በወቅቱ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 1 | በቁጥር | 48,473 | 52,857 | 45,413 | 68,530 | 45,413 | 52,071 |
| | | | | በወቅቱ የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.8 | በቁጥር | 24,441 | 29,775 | | 23,117 | | 6,658 |
| | | | | በወቅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.6 | በቁጥር | 19,001 | 26,548 | 26,548 | 26,548 | 26,548 | 26,548 |
| | | | | በወቅቱ የኤክሳይዝ ታክሳቸውን የሚያሳውቁ የግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.8 | በቁጥር | 475 | 502 | 502 | 502 | 502 | 502 |
| | | | | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ግብራቸውን በወቅቱ አሳውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮችን ማሳደግ | 0.3 | በቁጥር | 18,733 | 21,720 | 16,882 | 31,908 | 16,882 | 21,210 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| | | | | በወቅቱ አሳወቀው የንግድ ትርፍ ግብራቸውን የሚከፍሉ የግብር ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.1 | በመቶኛ | 44 | 65 | 65 | 65 | 65 | 65 |
| | | | | በወቅቱ አሳውቀው የተ/እ/ታክሳቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.2 | በመቶኛ | 37 | 41 | 41 | 41 | 41 | 41 |
| | | | | በወቅቱ አሳውቀው የኤክሳይዝ ታክስቸውን የሚከፍሉ ታክስ ከፋዮችን ምጣኔ ማሳደግ | 0.2 | በመቶኛ | 65 | 70 | 70 | 70 | 70 | 70 |
| | | | | ከቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎች ስሌት የተሰራላቸውን ምጣኔን ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 80 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | | የታክስ ከፋዮች ትምህርት፣ የኢንተለጀንስ ክትትል እና የኦዲት ሥራዎችን ማጠናከር (ክብደት = 15) | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት ግብራቸውን በወቅቱ የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች ድርሻ ማሳደግ | 5 | በመቶኛ | 38.65 | 41.09 | 37.17 | 46.56 | 37.17 | 40.73 |
| | | | | በሁሉም የታክስ ዓይነቶች በፈቃደኝነት የተሰበሰበ ግብር ከጠቅላላ የግብር ገቢ ድርሻ ማሳደግ | 10 | በመቶኛ | 81.4 | 86 | 86 | 86 | 86 | 86 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች | የግብ ክብደት | ዋና ዋና ተግባራትና ክብደት | ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | መነሻ (2014) | ዒላማ (2015) | በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 4 | ዘላቂ የመንግስት ገቢ ዕድገት ማረጋገጥ | 40 | ከሀገር ውስጥ ታክስ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ (ክብደት = 35) | ከቀጥታ ታክሶች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 15 | በብር | 112,142.39 | 153,959.79 | 25,886.48 | 60,702.49 | 24,931.03 | 42,439.79 |
| | | | | ቀጥታ ካልሆኑ ታክሶች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 10 | በብር | 83,372.59 | 112,304.79 | 23,972.44 | 27,059.84 | 27,365.81 | 33,906.69 |
| | | | | ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች የሚሰበሰብ ገቢ ማሳደግ | 5 | በብር | 696.66 | 688.21 | 162.71 | 180.42 | 164.31 | 180.77 |
| | | | | ከተሰበሰበው ገቢ የክልሎችን ድርሻ በወቅቱ ማስተላለፍ | 5 | በብር | 41,017.92 | 53,323.29 | 12,890.00 | 13,323.00 | 13,320.00 | 13,790.00 |
| | | | የታክስ ዕዳ አሰባሰብ አቅም ማጎልበት (ክብደት = 5) | ከአዲስ (60 ቀን) ካለሞላው ዕዳ የሚሰበሰብ የዕዳ መጠንን ማሳደግ | 4 | በብር | 32,578.43 | 33,089.89 | 7,157.87 | 8,004.77 | 8,778.92 | 9,148.33 |
| | | | | ከቆየ ዕዳ የሚሰበሰብ የዕዳ መጠንን ማሳደግ | 1 | በብር | 3,809.10 | 4,844.76 | 1,095.13 | 1,285.71 | 1,224.78 | 1,239.14 |

# ክፍል አራት

## 4 የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች

### 4.1 ዕቅዱን ለማሳካት በልዩ ትኩረት የሚሰሩ ስራዎች

የተቋሙን የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ለማሳካት ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ተለይተዋል፡፡

➲ ማስታወቅ እና ክፍያ ላይ የተጠናከረ ክትትል ማድረግ

ከማስታወቅ እና ከክፍያ አንጻር አራት ዋና ዋና ተግባራት ያሉ ሲሆን እነዚህም ያላሳወቁ ግብር ከፋዮችን መከታተል፣ ያሳወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ማጣራት እና ክትትል ማካሄድ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝሆልዲንግ ኤጀንቶች ላይ ክትትል ማድረግ እና የግብር ዕፎይታ መብት አጠቃቀምን አግባብነት መከታተል ናቸው፡፡ እነዚህን በውጤታማነት ከመስራት አንጻር በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ወቅታዊ እና የጠራ የግብር ከፋይ መረጃ መያዝ ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ በማስታወቅ እና በክፍያ ዙሪያ የሚሰሩ ስራዎች የበጀት ዓመቱን ገቢ እንዲሳካ ከማገዝ በተጨማሪ በዘላቂነት የህግ ተገዥነት ከማዳበር አኳያም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የማስታወቅ እና ክፍያ ክትትል ስራን ውጤታማ ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ ከግብር ከፋይ መረጃዎች በመነሳት በየወቅቱ እና በየግብር ዓይነቱ ማስታወቅ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች (ነባር እና አዲስን ጨምሮ) መለየት እና ከነዚህ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ገቢ (በየታክስ ዓይነቱ ከ70-80 በመቶ ገቢ የሚያስገኙ ግብር ከፋዮችን) በመለየት እንዲያሳውቁ እና ክፍያ እንዲፈጽሙ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በሚያሳውቁበት ወቅት መረጃ ወደ ሲስተም ማስገባት እና የታክስ ስሌት በወቅቱ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ወደ ሲስተም ያልገቡ እና ስሌት ያልተሰራላቸውን ማስታወቂያዎች እንዳይኖሩ ማድረግ ይገባል፡፡ ግብራቸውን ካሳወቁ ግብር ከፋዮች ውስጥ ባዶ፣ ኪሳራ እና አነስተኛ ግብር ያሳወቁ ግብር ከፋዮችን መከታተልም አስፈላጊ ነው፡፡ አነስተኛ ግብር ያሳወቁ የሚባሉት ግብር ከፋዮች ከዘርፋቸው አማካይ አንጻር በጣም ዝቅተኛ የሆነ መጠን ያሳወቁትን ነው፡፡ ከማስታወቅ ጋር በተያያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝሆልዲንግ ኤጀንቶች በወቅቱ ማስታወቃቸውን እና ክፍያ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ከፍተኛ መጠን ያለው ዊዝሆልዲንግ የሚሰበስቡ ተቋማት ላይ አተኩረን መስራት ያስፈልጋል፡፡

ያሳወቁ ግብር ከፋዮች ላይ ከሚደረገው የማጣራት እና ክትትል ስራ በተጨማሪ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮችን በመከታተል እና ግብራቸውን አሳውቀው እንዲከፍሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር

በዋና ዋና የታክስ ዓይነቶች (ንግድ ትርፍ፣ ተ.እ.ታ፣ ኤክሳይስ ታክስ እና የመሳሰሉት) ሳያሳውቁ የቀሩትን በመለየት እና ከፍተኛ ግብር ሊገኝባቸው የሚችሉ ዘርፎች እና ተቋማትን ቅድሚያ በመስጠት የክትትል ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም መንግስት የሰጠውን የግብር ዕፎይታ መብት አጠቃቀም አግባብነት መከታተል እና መብታቸውን አላግባብ የሚጠቀሙት ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የግብር ዕፎይታ መረጃ አደራጅቶ መያዝ፣ መብታቸው ያለቀውን ለይቶ ክፍያ መፈጸም መጀመራቸውን ማረጋገጥ እና መብታቸውን አላግባብ የሚጠቀሙት ላይ እርምጃ መውሰድ ዋና ዋና ስራዎች ናቸው፡፡

### ➲ የታክስ ኦዲት ስራን አጠናክሮ መቀጠል

የኦዲት ስራ በዋናነት የግብር ከፋዩን የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማሳደግ ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ ስራዎች አንዱ ሲሆን ከዕዳ ለሚገኘው ገቢም ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ውጤታማ የኦዲት ስራ ከማከናወን አንጻር ሶስት ቁልፍ ተግባራት ላይ ማተኮር ይመከራል፡፡ እነዚህም የኦዲት አፈጻጸምን ማሻሻል፣ የስነምግባር ችግሮችን መቅረፍ እና የኦዲት ጥራትን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

የኦዲት አፈጻጸምን ከማሻሻል አኳያ ትኩረት የሚሰጣቸው ስራዎች ውስጥ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸውን ግብር ከፋዮች አጠቃላይ ኦዲት ማድረግ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላላቸው የዴስክ እና ውስን ኦዲት ማካሄድ፣ የተ.እ. ታ፣ ኤክሳይስ ታክስ እና የንግድ ትርፍ ግብር የህግ ተገዥነት ክፍተት ባለባቸው ዘርፎች ላይ የውስን ኦዲት ማድረግ፣ ከግብር ከፋዮች ጋር የኦዲት ማጠቃለያ ኮንፈረንሶች ፍጥነት እና ውጤታማነት ማሻሻል እና የተገኙ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ጥቅም ላይ ማዋል እና በኦዲት ውስጥ ያሉ ቀዳዳዎች (Audit Leakages) ለመድፈን የቁጥጥር እና ክትትል ስራዎችን ማጠናከር፣ ግድፈት በሚታይባቸው ኦዲተሮች እና ግብር ከፋዮች ላይ የዕርምት ዕርምጃ በመውሰድ በከፍተኛ ሁኔታ የኦዲት ጥራትን በማረጋገጥ ከቅሬታ የጸዳ ውሳኔ መወሰን ይጠበቃል፡፡

### ➲ የቅሬታ እና የግብር ይግባኝ አፈጻጸምን ማሻሻል

የግብር ከፋዮችን ቅሬታ በአፋጣኝ እና በፍትሀዊነት ምላሽ መስጠት አገልግሎት አሰጣጡን ከማሻሻሉም በተጨማሪ ለገቢ ስኬት አስተዋጽዎው የጎላ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ስራዎች መካከል በቅሬታ ላይ ያሉ ፋይሎችን በመለየት በግምታዊ ዋጋ 80 በመቶ ያህል የሚሸፍኑ ፋይሎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣ የቅሬታ ውሳኔዎችን በመተንተን ለኦዲት እና ትምህርት ክፍሎች ግብረመልስ መስጠት እና የቅሬታ ውሳኔዎችን ዝርዝር መረጃ በመያዝ ያሉበትን ደረጃ ለአመራሩ እና ለሚመለከታቸው ክፍሎች በየጊዜው ማሳወቅ ይገኙበታል፡፡

### ➲ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም፣ ክትትል እና ቁጥጥርን ማጠናከር

በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ላይ በሚደረገዉ ክትትል እና ቁጥጥር ከተጨማሪ እሴት ታክስ የሚገኘዉ ገቢ ላይ ቁልፍ አስተዋጽዎ አለው፡፡ በመሆኑም ጠንካራ የክትትል እና ቁጥጥር ስራ በየደረጃው ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ከማሳካት አንጻርም ወቅታዊ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ

መረጃ ማደራጀት እና በስራ ላይ ያሉ እና የሌሉ ማሽኖችን መለየት፣ መረጃ የሚልኩ እና የማይልኩ ማሽኖችን መለየት እና አስፈላጊውን ትንተና እና ክትትል ማድረግ፣ በተመረጡ ግብር ከፋዮች ተቋማት በመገኘት የመሳሪያውን የአጠቃቀም ሁኔታ እና አዲስ ለሚያስገቡ ደንበኞች ሂደቱን በ3 ቀናት እንዲያጠናቅቁ ማድረግ በቁልፍ ስራነት ተወስዶ ሊሰራበት ይገባል።

### ➲ የታክስ ዕዳ አሰባሰብን ማሻሻል

በሀገር ውስጥ የዕዳ አሰባሰብ ስራ በ2014 በጀት ዓመት ለ36.39 ቢሊዮን ብር በላይ ተሰብስቦ ከበጀት ዓመቱ በሀገር ውስጥ ከተገኘዉ ብር 196.21 ቢሊዮን 18.55 በመቶ ያህሉን ሸፍኗል። በ2015 በጀት ዓመት የገቢ ዕቅድን ከማሳካት አንጻር የዕዳ አሰባሰብ ስራ ቁልፍ ድርሻ አለው። የዕዳ ዕቅድን ከማሳካት አንጻር የውሳኔ ማስታወቂያ የወጣባቸው ግብር ከፋዮች በ30 ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ ጥብቅ ክትትል ማድረግ፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና በተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡ የዕዳ ፋይሎችን መለየት፣ በክፍያ ስምምነት ውስጥ ያሉት ግብር ከፋዮች በወቅቱ የሚጠበቅባቸውን ክፍያ እንዲከፍሉ ክትትል ማድረግ እና ያልከፈሉት ላይ በታክስ ህጉ መሠረት እርምጃ መውሰድ፣ የተ.እ.ታ ዊዝሆልዲንግ ኤጀንቶች ዕዳ ውስጥ ከፍተኛ መጠን (80 በመቶ) የሚይዙትን በመለየት ጥብቅ ክትትል ማድረግ፣ በቅድመ እግድ ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች በ31ኛው ቀን የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ማድረግ እና የተጠናከረ ክትትል ማድረግ (በስልክ፣ በአጭር የስልክ መልዕክት እና በአካል)፣ ለእግድ የሚያስፈልጉ የግብር ከፋይ ዝርዝር መረጃ (አድራሻ፣ ተንቀሳቃሽ እና ቋሚ ንብረት፣ ወዘተ) ማደራጀት ላይ አተኩሮ መስራት ያስፈልጋል።

### ➲ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት

ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች ከመስራት ባሻገር የኢ-ማሳወቅ እና ኢ-ክፍያ ማስፋፋት፣ የሰራተኛውን እና ግብር ከፋዩን የስራ ቦታ ደህንነት ማረጋገጥ፣ የሰራተኛ ዕውቅናና ማበረታቻ ስራ ማካሄድ፣ ሀገራዊ የታክስ ንቅናቄን በስፋት መተግበር፣ ግብር ከፋዮችን ማስተማር፣ የመረጃ ጥራትን ማረጋገጥ እና የፌደራል ኦዲት ግኝት ማስተካከያዎችን በፍጥነት ማካሄድ ላይ በማተኮር መስራት ይጠበቃል።

## 4.2 የሪፖርት አቀራረብና የግንኙነት አግባብ

የተቋሙ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት በሶስት ዋና ዋና ስራዎች አማካኝነት የሚተገበር ይሆናል። እነዚህም የአፈጻጸም ሪፖርት ማከናወን፣ የክትትል እና ግምገማ ስራዎች እና የግብረ መልስ ስርዓት ናቸው። ስለሆነም የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ ለፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ገቢ ነክ ሪፖርቶችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል። በሌላ በኩል የተቋሙን ከፍተኛ አመራሮች ጨምሮ እና የተለያዩ ውስጣዊ አደረጃጀቶች የተቋሙን ሪፖርት ለስራቸው በግብዓትነት የሚጠቀሙት ይሆናል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ወቅታዊ፣ ጥራቱን የጠበቀ እና የተሟላ መረጃ የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል። ለዚህም እንዲረዳ የሪፖርት እና መረጃ አቀራርብ ስርዓት እንደሚከተለው ቀርቧል።

- **የየቀኑን የገቢ አሰባሰብ ሪፖርት:** ቅርንጫፎች እና ጉምሩክ ኮሚሽን (በየቅርንጫፉ) በየቀኑ የሰበሰቡትን ጠቅላላ ገቢ ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዲይሬክቶሬት በቀጣዩ ቀን እስከ ጠዋቱ አምስት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ያሳውቃሉ፡፡ ዳይሬክቶሬቱም የተቋሙን ዕለታዊ የገቢ አፈጻጸም ሪፖርት በማጠቃለል ለተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች እና ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በኢሜል እና አውትሉክ አድራሻቸው እስከ ቀኑ ስድስት ሰዓት ድረስ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡
- **ወርሃዊ የገቢ አሰባሰብ ሪፖርት:** የሀገር ዉስጥ ታክስ ቅርንጫፎች እና የጉምሩክ ኮሚሽን ወርሃዊ የገቢ አሰባሰብ ሪፖርት ወሩ ባለቀ በማግስቱ ያደረ ሂሳባቸውን አጠቃለው በአንድ ቀን ዉስጥ ጥቅል ወይም በገቢ ዓይነት ያልተከፋፈለ አፈጻጸማቸውን ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያሳውቃሉ፡፡ በተመሳሳይ በገቢ ዓይነት የተዘረዘረ ሪፖርታቸዉን በሁለተኛዉ ቀን ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መላክ ይኖርባቸዋል፡፡ የስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬትም በገቢ ዓይነት የተጠናቀረ የገቢ ሪፖርት ለተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች እና ለገንዘብ ሚኒስቴር የሚልክ ይሆናል፡፡
- **የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ:** ከገቢ ሪፖርት ውጪ ያሉ እና በተቋሙ ዓመታዊ ዕቅዱ ላይ የተቀመጡ ግቦች አፈጻጸም ሪፖርት ከስራ ዘርፎች፣ ከቅርንጫፎች እና ከጉምሩክ ኮሚሽን ወሩ ባለቀ 7 ቀናት ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የቀረቡለትን ሪፖርቶች በቀጣይ 3 ቀናት ውስጥ በማጠቃለል ለግብረ መልስ ለስራ ክፍሎች ይልካል፡፡ የስራ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች እና ተጠሪ ተቋማት ያላቸውን አስተያየት በ2 ቀን ውስጥ እንዲሰጡ ከተደረገ በኋላ የተሰጠውን ግብረ መልስ በማካተት የመጨረሻው ሪፖርት ወሩ ባለቀ በ10 ቀናት ውስጥ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል፡፡

  በተቋም ደረጃ በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁ ሪፖርቶች ከተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች በተጨማሪ ለውጭ አካላት የሚላኩ ይሆናል፡፡ ለውጭ አካላት በየሩብ ዓመቱ የሚዘጋጁት ሪፖርቶች ወር በገባ በ15 ቀናት ውስጥ የሚዘጋጁ ሲሆን ሪፖርቶቹም የተቋሙን የአመራር ግብዓት በማካተት የሚዘጋጁ ናቸው፡፡

## 4.3 የክትትልና ድጋፍ ስራዎች

ሁሉም አካላት በተዋረድ በተዘጋጀው ዕቅድ መሠረት አፈጻጸማቸውን መከታተልና መገምገም የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ክትትልና ግምገማው በስልክ ግንኙነት፣ በሪፖርት፣ በመስክ የሥራ ጉብኝት እና የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ይሆናል፡፡ በዋናነትም በየዳይሬክቶሬቶች እና በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የክትትልና የመስክ የሱፐርቪዥን ድጋፍ ሲደረግ በዕቅድ ዘመኑ የተቀመጡትን ዓላማዎች አፈጻጸም ቀጣይነት ለመከታተል ከምንጠቀምበት መንገድ አንዱ የክትትልና የሱፐርቪዥን ድጋፍ በመሆኑ በየሳምንቱ አርብ ዳይሬክቶሬቶች ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር እንዲሁም በየሳምንቱ ቅዳሜ በዙም የቴክኖሎጂ ስርዓት በየዘርፉ ግምገማና ድጋፎች ያደርጋሉ፡፡

በመሆኑም በዕቅድ የተያዙ ዓላማዎችን አፈጻጸም በተመለከተ በየዳይሬክቶሬቶች እና በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመስክ በአካል ተገኝቶ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በመስክ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬቶች እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመጎብኘት ስለአፈጻጸማቸው አግባብነት ካለቸው አመራሮችና ፈጻሚዎች ጋር ውይይት በማካሄድ እንዲሁም በአፈጻጸም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች በጋራ መፍትሄ በማስቀመጥ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**ወርሃዊ የአፈጻጸም ግምገማ:** በተቋም ደረጃ በሚዘጋጀው ወርሃዊ ሪፖርት ላይ በመመስረት የአፈጻጸም ግምገማ የሚደረግ ሲሆን የአፈጻጸም ግምገማው በዋናነት በገቢ እና ከገቢ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ወርሃዊ የአፈጻጸም ግምገማው በዘርፍ ደረጃ የሚካሄድ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በአዲስ አበባ የሚገኙ ቅርንጫፎችን በማሳተፍ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

**የሩብ ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ:** የሩብ ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ በዓመት ውስጥ ባሉት 4 ሩብ ዓመቶች (የመጀመሪያው ሩብ ዓመት፣ የ6 ወራት፣ የ9 ወራት እና ዓመታዊ) ያለውን የተቋሙ ዝርዝር አፈጻጸም ግምገማ የሚዳሰስበት ነው፡፡ በዚህ አፈጻጸም ግምገማ ላይ ሁሉም የስራ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች፣ የስራ ክፍሎች እና ጉምሩክ ኮሚሽን አፈጻጸማቸውን ገምግመው የሚገኙ ይሆናል፡፡ የአፈጻጸም ግምገማው ከ2-3 ቀናት የሚወስድ እና በየስራ ዘርፉ ዝርዝር የአፈጻጸም ግምገማ የሚካሄድበት እና ለቀጣይ ስራ አቅጣጫ የሚቀመጥበት ነው፡፡

**የአፈጻጸም ደረጃ ማስቀመጥ:** የተዘጋጀውን ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት በማድረግ ለስራ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች እና የስራ ክፍሎች በየሩብ ዓመቱ እና በዓመቱ ማጠቃለያ ላይ እንደየአፈጻጸማቸዉ የአፈጻጸም ደረጃ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## 4.4 የግብረ- መልስ ሥርዓት

የግብረ መልስ ስርዓቱ በሁለት ደረጃዎች የሚፈጸም ይሆናል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ በተቋሙ ተዘጋጅተው በተላኩ ዕቅዶች እና ሪፖርቶች ላይ ከውጫዊ አካላት በሚሰጡ ግብረ መልሶች ላይ በየደረጃው ማስተካከያ ወይም ማብራሪያ ማድረግ የሚጠበቅ ሲሆን በግብረ መልሱ መሠረት የተሻሻለ ሪፖርት ተዘጋጅቶ እንደገና ይላካል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በዋናነት ተቋሙ የአፈጻጸም ክፍተቶችን በየጊዜው እየለየ ለዘርፎች፣ ቅርንጫፎች፣ የስራ ክፍሎች እና ለጉምሩክ ኮሚሽን ግብረ መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በሚሰጠው ግብረ መልስ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል እና ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በተዘጋጀው የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ በአስፈጻሚ አካላት፣ በተገልጋዮችና ከባለድርሻ አካላት በሚሰጡ አስተያየቶችና ከሚደረጉ ውይይቶች ግብረ መልስ በማሰባሰብ ለቀጣይ የማስተካከያ እርምጃና በዕቅድ ዝግጅት ወቅት በግብዓትነት በመጠቀም ይሆናል፡፡ የሚሰጡት ግብረ መልሶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ማስተካከያ የማይወሰድባቸው ከሆነ ይህንኑ ያልፈጸመዉ አካል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

በዚህም መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት የሚሠጡ ግብረ መልሶችን መሠረት በማድረግ የተደራጀ የዕርምጃ አወሳሰድ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ዕርምጃዎችን በመውሰድ የአፈጻጸም ሪፖርት ይቀርባል፡፡ በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ በዋና ዋና ስራዎች በደረጃ የተነጻጸረ፣ በዋና ዋና ስራዎች ተመክሮ በማቀያየር እና በቀጣይ መከናወን ባለባቸዉ ተግባሮችና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ዙሪያ ክቡር ሚኒስትሩ በየሶስት ወሩ፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች በየወሩ የተደራጀ የጽሁፍ ግብረ መልስ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ዳይሬክቶሬቶች ይሰጣሉ፡፡

ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችም በተዋረድ በተመሳሳይ መልኩ በየወሩ የሚደረጉ የአፈጻጸም ግምገማዎችን ተከትለው የጽሁፍ ግብረ መልስ በየወሩ፣ የስራ ሂደቶች ለቡድኖች በየአስራ አምስት ቀኑ ግብረ መልስ መስጠትና መረጃውንም መያዝ ይኖረባቸዋል፡፡ በመጨረሻም የቡድን አስተባባሪዎች በየሳምንቱ የስራ ግምገማ ሲያደርጉ ለፈጻሚዎቻቸው ተከታታይነት ያለው የሳምንታዊ ተግባር አፈጻጸም አጫጭር ግብረ መልሶች መስጠትና መረጃውንም ለዉጤት ተኮር የምዘና ሰራዓት መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡